በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiop
Ministry of Education
Debre Markos University

# የጨረታ ማስታወቂያ

## DMU/NCB/ 11 /2016

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2016 በጀት ዓመት ከ "ክምፐተን - የእኛ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ 11" - ጀርመን በተደረገ ድጋፍ በምስራቅ ጎጃም ዞን ስዴ ወረዳ ሠረቀ ብርሃን ቀበሌ የ"እጨጌ ገሊላ-ክምፐተን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዙር" የመማሪያ ክፍሎች፣ የአስተዳደርና ቤተ-መጽሐፍት ሕንጻ እና መጸዳጃ ቤቶች (G+0 Building) በደረጃ GC Grade 5 or BC Grade 4 and above/ እና በላይ/ ባላቸዉ ተቋራጮች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም በጨረታዉ የሚሳተፉ ተጫራቾች ከዚህ በታች ማለትም፡-

1. በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና የቲን ምዝገባ ያላቸዉ፤ የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡
2. ለግንባታ ስራ የሚስፈልገዉን የሰዉ ሃይል፣ ማቴሪያል እና ማሽነሪወችን ሙሉ በሙሉ በራሱ አቅርቦ መስራት የሚችል፣ በደረጃ GC Grade 5 or BC Grade 4 and above /እና በላይ/ ያላቸዉ እና ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 90,075.00 (ዘጠና ሺህ ሰባ አምስት ብር) በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይንም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችሉ፤
3. ከላይ የተዘረዘሩተትን መስፈርቶች የሚያሟሉ የስራ ተቋራጭ የጨረታ ሰነዱን የጨረታ ማስታወቂያዉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወይንም Ethiopian Herald ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 21 ቀናት በስራ ሰዓት ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ወረደ ብሎ ሮሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7 ከሚገኘዉ ቢሯችን የማይመለስ ብር 300.00(ሶስት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. የጨረታዉን ፋይናንሻል ኦሪጅናል እና ኮፒ ፣ ቴክኒካል ኦሪጅናል እና ኮፒ ፣ የጫራታ ማስከበሪያ እንዲሁም አስፈላጊ ሰነዶችን ለየብቻ አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግ በእያንዳንዱ ፖስታ ላይ የአሰሪ መስሪያ ቤቱንና የተቋራጩን ሙሉ ስምና አድራሻ በመፃፍ ማህተም በማድረግ በተጠቃለለ አንድ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ተወዳዳሪወች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላት እና በማሸግ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ጋዜጣዉ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 21 ቀናት በኋላ በ22 ኛዉ ቀን እስከ ጥዋቱ 3፡59 ድረስ በተዘጋጀዉ ሳጥን ዉስጥ ማስገባት ሲኖርባቸዉ፤ ጨረታዉ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት 4፡30 ላይ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ዉስጥ ይከፈታል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በጨረታዉ ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታዉ ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታ ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡
6. አሸናፊዉ ድርጅት አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7 ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የዉል ማስከበሪያ በማስያዝ በ5 ቀናት ዉስጥ ዉል መያዝ ይኖርበታል፡፡

የበለጠ መረጃ ለማግኘት ስልክ ቁጥር፡- +25158-771-6691/+25158-178-0037 ደዉለዉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- ❖ የግንባታ ቦታው በደብረ ማርቆስ - ጮቄ - ከርነዋሪ - ሞጣ መስመር ላይ የሚገኝ ሲሆን ከደብረ ማርቆስ 65 ኪ.ሜ ከሞጣ ደግሞ 35 ኪ.ሜ አካባቢ ላይ ነው፡፡
- ❖ ጨረታ መክፈቻ ቀኑ የበዓል ቀን ወይም ቅዳሜ እና እሁድ ከሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
- ❖ ዩኒቨርሲቲዉ ጨረታዉን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡

**ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ**

☎ 058-771-6691 Fax: 058-771-1764 ✉269

መልስ ሲጽፉልን እባክዎን የእኛን ቁጥር ይጥቀሱ
In replying Please Quote our Ref.No.